


# የልጃችሁ በነፃ የመስማት ችሎታ ምርመራ



ጤነኛ የመስማት ፕሮግራም አላማ የዕድሜ ልክ የመስማት ችሎታ ጉድለት ኖሮባቸው የተወለዱትን ህፃናት ለማወቅ ነው:: ይህ የነፃ አገልግሎት ሲሆን እስከ 2006 መጨረሻ ድረስ ይህ አገልግሎት ለሁሉም ኩዊንስላንድ (Queensland) ውስጥ ለሚወለዱ ህፃናት ይሰጣል::

Queensland Government
Queensland Health

## የመስማትና የመናገር ማረጋገጫ ችዎእድሚያቸው...

### ከትውልድ እስከ 3 ወራት

- ☐ የለመዱትን ንግግር ወይም ድምጽ ሲሰሙ ይረጋጋሉ
- ☐ ድንገተኛ ድምጽ ሲኖር ይደነግጣሉ ወይም ይዘላሉ

### ከ3 እስከ 6 ወራት

- ☐ ራስን ወይም ዐይንን የሚማርክ ድምፅ ወደሚሰሙበት አቅጣጫ ያዞራሉ
- ☐ የሚያዳምጡ ይመስላሉ
- ☐ በድምፅ በቀላሉ ይነቃሉ
- ☐ ንግግር የሚመስል ድምፅ ማሰማት ይጀምራሉ

### ከ6 እስከ 12 ወራት

- ☐ ቀላል እንደ «ኖ» ('no') እና ባይባይ ('bye-bye') የመሳሰሉ ቃላቶች ይገባቸዋል
- ☐ የንግግር ድምፅ መቅዳት ይጀምራል
- ☐ ራሳቸውን በቀስታ ድምፅ ወደሚሰሙበት አቅጣጫ ያዞራሉ

### ከ12 እስከ 18 ወራት

- ☐ በየሳምንቱ የበለጠ ቃላት የሚገባቸው ይመስላሉ
- ☐ ሲጠየቁ ወደ ሰችዎኖ የሠውነት ክፍሎች ወይም ወደ መጫወቻች ያመለክታሉ
- ☐ ቀላል የንግግር ትዕዛዛትን ይከተላሉ ለምሳሌ: ቁጭ በል

የልጃችሁ የመስማት ችሎታ የሚያሳስባችሁ ከሆነ የልጃችሁን ሀኪም ወይም የአከባቢያችሁን የጤና ክሊኒክ አባል አነጋግሩ::

# የልጃችሁ የመስማት ችሎታ ምርመራ

ከመጀመሪያዎቹ የትውልድ ወራት ጀምሮ ጤነኛ የመስማት ችሎታ ለልጃችሁ የንግግርና የቋንቋ መዳበር በጣም አስፈላጊ ነው:: ከ1000 ህፃናት መከከል አንድ ወይም ሁለት ልጆች ከበድ ያለ የመስማት ችሎታ ጉድለት ይደርስባቸዋል::

የመስማት ችሎታ ጉድለት ቶሎ ከልታወቀ የልጃችሁ የንግግርና የቋንቋ ችሎታ መዳበርና የወደፊት ትምህርት ቤት ገብቶ የመማር እድሉን ሊያውክ ይችላል::

የመስማት ችሎታ ምርመራ ቀጠሮ

..........................................................................

ቀን ..................................................................

ሰዓት ...............................................................

ቦታ ..................................................................

## ከልጅ የጤንነት ምርመራ አንዱ ክፍል

ጤነኛ የመስማት ፕሮግራም አላማ የዕድሜ ልክ$_x$ የመስማት ችሎታ ጉድለት ኖሮባቸው የተወለዱትን ህፃናት ለማወቅ ነው:: ይህ የነፃ አገልግሎት ሲሆን እስከ 2006 መጨረሻ ድረስ ይህ አገልግሎት ለሁሉም ኩዊንስላንድ (Queensland) ውስጥ ለሚወለዱ ህፃናት ይሰጣል::

ልጃችሁ ከተወለደ/ች በኋለ ቁጥሩ በዛ የለ የጤና ምርመራ ይደረግላቸዋል:: ከእነዚህም ምርመራች አንዱ የመስማት ችሎታ ጉድለትን መመርመር ይሆናል:: ይህ ምርመራ ከትውልድ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ይደረጋል:: ይህ ምርመራ አንቺና ልጅሽ ሆስፒታል ከመልቀቃችሁ በፊት ከልተደረገነ ልጅሽ እንደ ተመላላሽ ታከሚ ሆኖ ቶሎ እቤት ከገባችሁ በኋላ ይህንን ምርመራ ማግኘት ይችላል::

## እንዴት ነው ምርመራው የሚደረገው?

የመስማት ችሎታ ምርመራ ልጃችሁን አይጎዳውም:: ነርስ ወይም ይህንን ምርመራ ለማከሄድ የሰለጠነ ሰው ህፃኑ ፀጥ ባለ ወይም በተኛ ጊዜ ምርመራውን ያደርጋሉ:: ብዙ ትናንሽ ሽፋኖች (pads) በህፃኑ ራስ ላይ በቀስታ ይደረግና ለስላሳ ጆሮ ላይ የሚደረግ ማዳመጫ በቀስታ እያንዳንዱ ጆሮ ላይ ይቀመጣል:: ለስላሳ የቃጭል አይነት ድምፅ በህፃኑ ጆሮ ላይ በተደረጉ ማዳመጫች አማከይነት በህፃኑ ጆሮ ውስጥ እንዲጫወት ይደረጋል:: ህፃኑ ለድምፁ የሰጠው መልስ ጆሮው ላይ በተቀመጡት ትናንሽ ሽፋኖች ላይ ይመዘገባል::

## መቼ ነው ውጤቶቹን የማውቀው?

የምርመራው ውጤት ወዲያውኑ ይታወቃል፣ ውጤቱም በህፃኑ የግል የጤና መዘገብ ላይ ይመዘገባል:: ምርመራውን የሚያከሂደው ሰው ስለውጤቱ ከአንቺ ጋር ይወያያል:: እርግጠኛ ያልሆንሽበት ነገር ከለ ጥየቂ ጠይቂ::

## ምርመራው ምን መረጃ ነው የሚሰጠን?

ለእይንዳንዱ ዓመት ምርመራው ወይ የ ‘pass’ ውጤት ወይም ‘refer’ ውጤት ይሰጣል:: ይህ ምርመራ ስለ ልጃችህ የመስማት ችሎታ ዝርዝር መረጃ አይሰጥም::

## ውጤቱ አልፎዋል (pass) ሲሆን ምን ማለት ነው?

በሁለቱም ጆሮዎች ላይ ውጤቱ አልፈዋል ኪሆነ ልጃችሁ የንግግርና የቋንቋ መዳበርን የሚያውክ የመስማት ጉድለት ላይኖርበት/ባት ይችላል::

ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ህፃናት ምርመራውን ሊያልፉ ይችላሉ፤ሆኖም ግን ረዘም ያለ ጊዜ ወስደው የሚከሰቱ የመስማት ችሎታ ጉድለት አይነቶች እንዳሉ ይታወቃል:: የእናንተ ልጅ የዚህ ዓይነት ሁኔታ ከገጠመው የመስማት ችሎታ ምርመራ ከጆሮ ሀኪም (Audiologist) ጋር እንዲያደርግ ዕድል ይሰጠዋል:: ይህም አንዳንድ ጊዜ ከመጀመሪያው የልደት በዓል በፊት ይሆናል:: የዚህ ምርመራ ወቅት የሚወሰነው እንደልጁ ልዩ ፍላጎት ይሆናል:: በጣም ጥቂት የሆኑ ልጆች የዚህ ዓይነት የመስማት ችግር የሚከሰትባቸው ሲሆንነ ለእናንተም ልጅ ይህን፣ ምርመራ ማድረግ ጠቃሚ ነው::

የህፃናት ልጆች የመስማት ችሎታ ከጊዜ ጋር እንደሚለወጥ አስታውሱ:: በማንኛውም ሰዓት የልጃችሁ የመስማት ችሎታ የሚያሳስባችሁ ከሆነ ሐኪማችሁን ወይም የአከባቢያችሁን የጤና ክሊኒክ አባል አነጋግሩ:: የመስማት ችሎታ ምርመራ በህፃናትና በልጆች ላይ በማንኛውም ዕድሜ ሊደረግ ይችላል::

## ውጤቱ መመራት (refer) ሲባል ምን ማለት ነው?

የምርመራው ውጤት መመራት (refer) ሊባል የሚችልበት ሁኔታ የተለያየ ቁጥር ባለቸው ነገሮች ሊፈጠር ይችላል::

- ሕፃኑ በምርመራው ወቅት ያልተረጋጋ ከነበረ
- በምርመራው ወቅት የሚያስተጋባ ድምፅ ከነበረ
- ልጃችሁ ከተወለደ በኋላ ጆሮው ላይ ፈሳሽ ሊኖረው ወይም ጊዜያዊ መደፈን ሊያጋጥመው ይችላል::
- ቁጥራቸው ትንሽ የሆኑ ህፃናት ጊዜያዊ ወይም የዕድሜ ልክ የመስማት ችሎታ ጉድለት ሊኖራቸው ይችላል:: የጉዳቱ መጠን ከቀላል እስከ ከባድ ድረስ ሊለያይ ይችላል::

የልጃችሁ የመጀመሪያ ምርመራ ጊዜ በአንዱ ወይም በሁለቱም ጆሮዎች ላይ መመራት (refer) የሚል ውጤት ከሳየ ሁለተኛ የመስማት ችሎታ ምርመራ በሁለቱም ጆሮዎች ላይ ይደረጋል::

የልጃችሁ ሁለተኛ ምርመራ መመራት (refer) የሚል ውጤት በአንዱ ወይም በሁለቱም ጆሮዎች ላይ ከሳየ ልጃችሁን የጆሮ ሐኪም (Audiologist) ጋር እንድታስመረምሩ ዕድል ይሰጣችኋል:: ይህንንም በዝርዝር የሚገልፅ ተጨማሪ ፅሑፍ ይሰጣችኋል::

## ተጨማሪ መረጃ ከየት ነው የማገኘው?

ስለ ልጃችሁ የመስማት ችሎታ ምርመራ የበለጠ መረጃ ከፈለጋችሁ የአከባቢያችሁን ሆስፒታል፣ የልጃችሁን ሐኪም ወይም የአከባቢያችሁን የጤና ክሊኒክ አባል አነጋግሩ::







Language: Amharic

LAST UPDATED: February 2006